# የወሰን ግጭቱ፤ ከማስኤና ወጡ አንፃር

መዝገቡ ዋኘው 09-28-17

ሀገራዊ ሰላምን የማጠበቅና የማስጠበቅ ስራና ኃላፊነት በመንግስት ላይ ብቻ የሚጣል አይደለም፤ በዋነኛነት የሕብረተሰቡ ኃላፊነት ነው፡፡ መንግስት ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲፈጠሩ የአደጋው ስፋትና ጥልቀት አሰሳቢ ሁኖ ሲገኝ ጣልቃ በመግባት ሰላምን በማስከበረ ሚረጋጋት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በቅርቡ በሶማሌ ክልልና በኦሮሚያ በወሰን ጉዳይ የተነሳው አለመግባባት ደረጃው እየጨመረ፤ መልኩን እየቀየረ በመምጣቱ የፌደራሉ መንግስት ጸጥታና ሰላምን ለማስከበር የሚገባበትን ሁኔታ ፈጥሮአል፡፡

ጉዳዩ በየእለቱ መልኩን እየቀየረ ከመሄዱ በፊት ችግሩን ለመፍታት የሁለቱን ክልላዊ መንግስታት መሪዎች የፌደራል ሚኒስትሩ ሰብስበው በማነጋገር ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈታ ለማድረግ ጥረት ያደረጉ ሲሆን፤ በሂደቱም ተስፋ ሰጪ ሁኔታዎች ተሰተወለዋል። ዳግም ሁኔታው የተለወጠው በወሰኑ አካባቢ ተደጋጋሚ ግጭቶች በማከሰታቸው ምክንያት ለበርካታ ዜጎች ሕይወት መጥፋትና የዜጎችንም መፈናቀል አስከትለዋል፡፡

ይህን የማሰለው ክስተት የሚያጋጥም ቢሆንም ለፈታ የሚገባው በሰላማዊ ወይይትና ንግግር ብቻ መሆን ነበረበት፡፡ ይህንን ሁኔታ ሆን ብሎ እንዲባባስና ከመንገድ እንዲወጣ ያደረጉት ግለሰቦች በምንም መልኩ ከተጠያቂነት ሊወጡና ሊያመልጡ አይችሉም፡፡ ለረዥም ዘመናት በፍቅር፣ በመቻቻልና በመካባበር ተጋብቶና ተዋልዶ የአንዱን ቋንቋ ሌላው እየተናገረ የኖረውን ሕዝብ ማባላትና ደም ማፉሰስ ጤነኛ ሰዎች ያደርጉታል ተብሎ አይታመንም፡፡

ቀጣናው ራሱን የቻለ የተለየ ችግር ያለው ከመሆኑም አንጻር በስፋት ሊሚመኑ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ ይሄን ከስሩ የማጣራትና የሚፈተሹ በተገኘወም ተጨባጭ ማስረጃ ማስረት እርምጃ የመወሰዱ ግዴታና ኃላፊነተ የፌደራል መንግስት ነው የሚሆነው፡፡ ጉዳዩ አንዱ ሌላኛውን በመወንጀል ብቻ የሚያበቃ አይደለም፡፡ በእርግጥ *ከዚህ ግጭት ጀርባ የክልላዊ መንግስታቶቹ ታጣቂዎች ብቻ ናቸው ወይ ያሉት?* የሚለውም በጥልቀት መፈተሸ አለበት፡፡

ለምን ቢባል ቀድሞ በነበሩት ረዥም አመታት እንዲህ አይነቱ የገፋ ችግር አልተከሰትም ነበር፡፡ ጥፋትና ግድያ ፈጻሙ የሚባሉት የሶማሌ ክልል ታጣቂዎች ናቸው ወይንስ የእነሱን ስም በማጠቀም ምናልባትም ዩኒፎርም በመልበስ ሌሎች ኃይሎች (የአልሻባብና የኦብነግ ታጣቂዎች) የሕዝብ ለሕዝብ ግጭት እንዲፈጠር፤ በአካባቢው ሰላምና ሚረጋጋት እንዲጠፉ፤ በዚህም ለእነሱ የተደላደለ የመፈንጫ መሬት ለማግኘት የተጠቀሙት ስልት ይሆን? ብሎ በምናልባታዊነት መፈተሽም ተገቢ ነው፡፡

ኢትዮጵያን በቀንደኛ ጠላትነት የሚፈርጃትና በእስከአሁኑ ተጨባጭ ሁኔታ የመግቢያ ቀዳዳ ያላገኙት አልሻባብ እና ኦብነግን የመሳሰሉ የሽብር ድርጅቶች አዲስ ስልት ነድፈው እየተጠቀሙት ቢሆንስ? የሌሎች

የውጭ ኃይሎች እጅ በአባባሺነትና በአቀጣጣይነት ከጀርባ ቢኖሩበትስ ብሎ ማጠየቅ ለሀገር ሕልውና ሲባል ግድ ይላል፡፡

በዚህ ቀጠና ወስጥ የተፈጠረወን ክፍተት በመጠቀም ሕዝብን ከሕዝብ በማጋጨት የኢትዮጵያን ፈጣን ልማትና እድገት ለመግታት በተለይም የታላቁ ሕዳሴ ግድብን ስራ ለማጨናገፍ በስትራቴጂ ደረጃ የረዥም ግዜ እቅድ ነድፈው የሚንቀሳቀሱት ግብጽና ኤርትራ ይህንን የግጭቱን አካባቢ አይጠቀሙበትም ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። ይሄንንም ሚዛኑ ግድ ይለናል፡፡

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ሶማሌወም ሆነ አሮሞው ረዥም ዘመናት አብረው የኖሩ ከመሆናቸው አንጻር ቀድሞ ይታይ እንደነበረው ማጠነኛ አለመግባባቶችና ግጭቶች ቢፈጠሩም በቀላሉ በሽማግሌዎች ሊፈቱ ይችሉ የነበሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ የግጭቱ ማጠን በገዘፈ ደረጃ ማስከተሉ የዜጎችን ሞትና ከመኖሪያቸው መፈናቀልን ማስከተሉ ሲታይ የግድ ከእነዚህ ታሳቢ ግምቶች በመነሳት የእይታ አድማሳችንን አስፍተን መመልከት ይጠበቅብናል፡፡ ለምን ሆነ? ለምን ተደረገ? ገፊ ምክንያቶቹ ምንድናቸው? የሚሉትን ደጋግሞ መመርመር ግድ ይላል፡፡ ያለው ሁኔታ ከሕዝብ ማጋጨት፣ ከሰላም ማጣትና መደፍረስ ማጠቀም የሚፈልጉ ኃይሎች ስለመኖራቸው አመላካች ነው፤ በምንም መልኩ ወደዚህ ደረጃ ሚደግና ማስፋት ያልነበረበት ሁኔታ ነበርና፡፡

በአሁኑ ሰአት ግጭቱን ለመፍታት መንግስት መከላከያና የፌደራል ፈጥኖ ደራሽ ልዩ ኃይል በስፍራው እንዲገባ አድርጎአል፡፡ የሚያጋጋት፣ የተፈናቀሉትን የመርዳትና የመልሶ ማቋቋም፣ በሀገር ሽማግሌዎች የማስማማት፣ ከሕዝቡም ጋር በየደረጃው ወይይቶችን በማድረግ ችግሩን ለመፍታት ከፍተኛ ስራ በማስራት ለይ ይገኛል፡፡

የተከሰተወን ሁኔታ መነሻ በማድረግ በተለይ በሶማሌ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ የተሰጠው እጅግ ኃላፊነት የጎደለው መግለጫ በእርግጥ እነዚህ ሰዎች ክልልና ሕዝብ የሚመሩ ናቸው ወይ የሚለው ጥያቄ የሕዝብ ማነጋገሪያ ሆኖ እንዲከርም አድርጎአል፡፡ የሁለቱም ክልሎች ኃላፊዎች የተሸከሙት የሕዝብ አደራና ኃላፊነት እንደመሆኑ ማጠን የፌደራል መንግስት ሳይገባም እርስ በእርስ ተገናኝተው ተነጋግረው ችግሩን ሊፈቱት ይገባቸው ነበር፡፡ ይህም ካልተቻለ ጉዳዩን በጨዋነት በስነስርአት ፈትሸው የፌደራሉ መንግስት በጋራ አነጋግሮ የሚፈታው ጉዳይ ነበር የሚሆነው፡፡

በየክልሎቹ ኮሙኒኬሽን ቢሮዎች የወጡት መግለጫዎች ይባስ ጉዳዩን ወደከረረ ጫፍ እንዲነጉድ ያደረጉ ነበሩ፡፡ ይሄንን ማስረትና ዋቢ ያደረገው የውጭው ሚዲያ የተፈጠረወን ችግር የባሰ የሚቀጣጠል ሰራ ሰርቶአል፡፡ ይህ አዝማሚያ ሀገሪቱን ወደ ቀወስ ወስጥ ለመክተት በታቀደ መልኩ እየተሰራ ያለስራ ለመኖሩ በግልጽ አመላካች ነው፡፡

ትላልቅ የተባሉትን ሀገራት ለመፍረስና ለማጥታተን ያበቁአቸው በትንሹ ሊቆም የሚችለወን ችግር እያሰፉ፣ ሕዝቡን እያነሳሱ፣ ጥላቻ እየዘሩ፣ እርስ በእርሱ እያፋጁና እያባሉት በሚዲያ ሜነት የተጀመረው

የማዋጋት ስራ በሕዝብ እልቂት ደም መፋሰስና ስደት በሀገራት ሚፈራረስ ተደመድሙ፡፡ ይህ አይነቱ እኩይ የአቀጣጣይነት ስራ ለሕዝብም ለሀገርም ሕልወና አይበጅም፡፡ ተጎጂው ሕዝብና ሀገር ናቸው፡፡

አለም አቀፉ ሚዲያ እንዲሁም አክራሪው ጽንፈኛ ኃይል መላ ትኩረታቸውን በኢትዮጵያ ሶማሌ እና በኦሮሚያ ከወሰን ጋር ተያይዞ በተከሰተው ግጭት ላይ በማድረግ የበለጠ ብጥብጥና ግጭት የሚባባስበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሲዳከሩ ከርመዋል፡፡ የበለጠ መተራመስ፣ ግጭትና ደም መፋሰስ እንዲፈጠር ዛሬም በስፋት በማስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ምንም ተፈጠረ ምን የሀገሩን ሰላምና ደሕንነት ነቅቶ የሚጠብቅ ሕዝብና መንግስት ስላለ የአሰቡትን ሊያሳኩ አይችሉም፡፡

ችግሩን የማጉላት ስራ ዛሬም በተለያየ የውጭ ሚዲያዎች በአክራሪወና ጽንፈኛው ኃይል ድረገጾች እንዲሁም በፌስቡክ አማካኝነት እንደቀጠለ ይገኛል፡፡ ይህ የሀገርን ሰላምና ሚጋጋት የሚደፈርስ ስራ ባለቤት ያለው መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ ለኢትዮጵያና ለሕዝብዋ በምንም መልኩ አይበጅም፡፡ የመፍትሄው አካል ሳይሆኑ ዋነኛ ተልእኮአቸው ሀገሪቱን ትርምስ ወስጥ መክተት ስለሆነ ሊምከት ይገባዋል፡፡ በሀገር ሕልወና ላይ የተነጣጠረ አደጋም ነው፡፡

ግጭቱ በምንም መልኩ የሁለቱን ክልሎች ወንድማማች ሕዝቦች አይወክልም፡፡ ሁለቱም ሕዝቦች ለዘመናት የዘለቀ የአብሮነትና የመቻቻል እሴት ያላቸው በመሆኑ ግንኙነታቸው በጊዜያዊ ችግር ሳቢያ አይደናቀፍም፡፡

ዛሬም የክልሎቹ ሚዲያዎች ቆም ብለው ራሳቸውን ሚፈተሽ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሕግ ስርአትና መንግስት ባለበት ሀገር ችግሮችን በስርአቱና በአግባቡ መፍታት እየተቻለ እርስ በእርስ መናቆሩ ይህንን ለሚፈልጉት ኃይሎች ጥይት አቀባይ መሆኑ ለሕዝባቸውም ለሀገሪቱም የሚጠቅም መሆኑን ሊያውቁት ይገባል፡፡ የአንድ ሀገር ዜጎች መሆናቸውንም የረሱበት ሁኔታ ታይቶአል፡፡ አንዱ በሌላው ላይ የጠለቀ ጥላቻ እንዲያድርበት የሚድረጉ ተግባር መጨረሻው የከፋ ጥፋትና ወድመትን ከማስከተል ወጪ የረባ ፋይዳ የለወም፡፡ ለሀገርም ለሕዝብም የሚበጅ አይደለም፡፡ ለሁለቱ ወንድማማች ሕዝቦችም ሆነ ለመላው አገራችን የሚበጅ የጥፋት መንገድና እጅግ አደገኛ አዝማሚያ በመሆኑ በፍጥነት ሊገታ ይገባዋል፡፡

በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች የተነሳውን ግጭት በመቀስቀስና በማባባስ እንዲሁም የዜጎችን አካል በማጉደልና የሰው ሕይወት በማጥፋት የሚጠረጠሩ ግለሰቦችም ሆኑ የፀጥታ ኃይሎች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ ማጠራጠር አይገባም፡፡

በአብዛኛው የሕዝብ ማናኛ ብዙሐን በተለያየ ደረጃ የፌደራል ስርአቱንና የሕዝቦችን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥሉ በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬ የሚፈጥሩና ግጭትን የሚቀሰቅሱ መግለጫዎችንና ዘገባዎችን ከማስራጨት ሊቆጠቡ ይገባል፡፡ ይህ እያቆጠቆጠ በመምጣት ላይ የሚገኘው አደገኛ አዝማሚያ ጋዜጠኝነት ከሚጠይቀው ስነምግባር፣ ከማናኛ ብዙህንና ከሚጃ ነጻነት ሕጉ እንዲሁም ከአለም አቀፍ ሕጎችም ጋር ሚጭ በሚጭ የሚጻረር በመሆኑ ጥንቀቄ ሊያደርጉበት ይገባል፡፡

የሚዲያ ባለሞያዎች ጉዳዩ በቀጥታ ከሀገራዊ ደሕንነትና ሰላም ጋር የተገናኘ በመሆኑ ይህም በሕጎች ላይ በግልጽ ሰፍሮ የተቀመጠ ስለሆነ ሊያጤኑት ግድ ይላል፡፡ ችግሩ መንገደና አቅጣጫ ስቶ ቢሄድ ጥፋት፣ እልቂትና ወድመት ቢከሰት ዜጎቹም የራሳችን ወንደሞች፤ ሀብቱም ንብረቱም የእኛው፤ የምንጎዳወም የምናዝነወም የምንጸጸተወም እኛው ነን፡፡ የሚደሰቱና የሚጨፍሩት ደግሞ ጠላቶቻችን ናቸው፡፡ ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ፡፡ ይሄን የጥፋት ድግስ ሰብረን ለማቆም ሚባረብ የሁሉም ዜጋ ቀዳሚ ስራ መሆን ይገባዋል፡፡

ባጠቃላይ ይህን በኢትዮጵያ ሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልሎች ከወሰን ጋር በተያያዘ የተፈጠረወን ግጭት ለመቆጣጠር፤ የቀደሞወን ሰላምና መረጋጋት ለማስፈንና አጥፊዎችን ተጠያቂ ለማድረግ ልዩ ልዩ ተግባራት በማንግስት በኩል እየተከናወኑ ይገኛሉ፡፡ ከኃይማኖት አባቶችና ከሀገር ሽማግሌዎች ጋር የጋራ ወይይት እየተደረገ ነው ሲሆን፤ ተፈናቃዮችን ሚልሶ የማቋቋም፤ ሕዝባዊ ወይይቶችን የማካሄድና ሌሎች የሚረጋጋት ተግባራት በስፋት እየተሰሩ፤ የፌደራል የፀጥታ ኃይሎችም የሕዝቡን ሰላም በማጠበቅና በሚረጋጋት ሥራ ላይ ተሰማርተው ሕግና ደንብ እያስከበሩ መገኘታቸው የሚያበረታታ ሲሆን ለስኬቱም አጠቃላይ ህዝቡ ከጎናቸው ሊቆም ይገባል፡፡